የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፵፭
አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 45
ADDIS ABABA 14th July, 2014

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፭/፪ሺ፮

ለአዲስ አበባ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ የተገኘውብድርስምምነትማፅደቂያአዋጅ....... ገጽ ፯ሺ፬፻፴፫

## CONTENTS

PROCLAMATION NO. 845/2014

Agency Francaise De Developpement cred facility Agreement for financing the Solid We Management Addis Ababa New Sanitary Land Fi Project Ratification Proclamation ............ Page 743

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፭/፪ሺ፮

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአዲስ አበባ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፳ ሚሊዮን ዩሮ (ሃያ ሚሊዮን ዩሮ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል እ.አ.አ ዲሴምበር ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 845/2014

## A PROCLAMATION TO RATIFAY THE CREDIT FACILITY AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND AGENCE FRANCAISE DE DEVELOPPMENT

WHEREAS, Credit Facility Agreement between the Federal Democratic Republic o Ethiopia and the Agence Francaise D Developpement stipulating that the Agenc Francaise De Developpement shall make availabl to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit facility in an amount of Twenty millior EURO (EURO 20,000,000) for financing the Solic West Management Addis Ababa New Sanitary Land Fill Project was signed in Addis Ababa, or the 19th day of December 2013;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 5th day of July,2014;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለአዲስ አበባ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፭/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል እ.አ.አ ዲሴምበር ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፫ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር CET 1041 01 N የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. **የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፳ ሚሊዮን ዩሮ (ሃያ ሚሊዮን ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Agence Francaise De Developpement credit facility Agreement for financing the Solid West Management Addis Ababa New Sanitary Land Fill Project Ratification Proclamation No.845/2014".

2. **Ratification**

The Credit Facility Agreement signed in Addis Ababa, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Agence Francaise De Developpement on the 19th day of December 2013 Agence Francaise De Development Agreement No. CET 1041 01 N is hereby ratified.

3. **Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit Facility amount of Twenty million EUROS (EURO 20,000,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Facility Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 14th day of July,2014**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት